አጢታይዘር

አስቲ ወደ መጽሐፉ ዋና ክፍል ከመግባታችን በፊት እነኚህን አጫጭር መልዕክቶች እንቅመስ -ምናልባት የንባብ ፍላጎታችንን ይከፍቱልን እንደሆነ ብዬ።

- ማታ ላይ ስንተኛ በፈቃደኝነት ትንሹን ለመሞት ብለን መኝታችንን እናነጥፋለን። በፈቃደኝነት ሳይሆን ተገደን የምንሞተው ትልቁ ሞት ከፊታችን አለ። ያኔ ሰዎች ናቸው መተኛችንን የሚደለድሉልን።

- የመሬት ሥር ቤታችንን የሚያሳምረው የዛሬ ሥራችን ነውና ለዛሬ መኝታችን እንደምንጨነቀው ሁሉ ለነገ ማረፊያችንም እንጨነቅ።

- ዳግመኛ የማትነሱበት እንቅልፍ ሊሆን ይችላልና ሁሌም ከመተኛታችሁ በፊት ቀልባችሁን ንፁህ አድርጉ፤ የበደላችሁን ሁሉ ይቅር በሉ። ያኔ ጥሩ እንቅልፍ ይወስዳችኋል፤ ሌሊታችሁም ሰላማዊ ይሆናል።

- ይቅር ባይነት የአላህ ባህሪ ነው። አላህ በሱ ባህሪ የተገለጡትን ሁሉ ይወዳል፣ ይቀበላል።

- በሕይወት በመቆየታችን ጠዋት ማልደን ተነስተን፣ ማታ ላይም አምሽተን አልሐምዱ ሊላህ... ለማለት ቻልን። ‹አልሐምዱ ሊላህ!› የምትለው ቃል አባታችን አደም (ዐ.ሰ.) ምድር ላይ የተናገሯት የመጀመሪያዋ ቃል ናት።

- “ከአምስቱ ሶላቶች መካከል አንደኛዋ የመጨረሻችሁ ልትሆን ትችላለችና እያንዳንዷን ሶላታችሁን አሳምራችሁ ስገዱ” ብለዋል ዓሪፎቹ።

- ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የሞቱት ሁሉ እንደኛው ለዛሬ ያሳደሩት፣ ለነገም ያለሙት ዕቅድና ዓላማ ነበራቸው ።

- ማልደን ተነስተን እንሮጣለን፤ ስንሮጥ ውለንም አንገባለን፤ ዕድሜያችን ያልቃል፣ ሓጃዎቻችን ግን ፈጽሞ አያልቁም።

- ሌሊቱን ሳይተኛ ያነጋ ሁሉ በምን እንዳነጋ መልሶ ይገምግም። በመጥፎ ካነጋ አይድገመው፤ በጥሩ ካነጋ ይመላለስበት።

- ከሱብሒ በፊት የሚደረጉ ዱዓዎች ዒላማቸውን አይስቱም። በርቱና ተኩሱ። ለአላህ ስገዱ፤ አጎንብሱ።

- መቃብር ስትወርዱ አዚያ ትላልቅ ጥያቄዎች አሉ። ጥያቄዎቹን ጠንቅቃችሁ እወቁ። ትከከለኛውን መልስም አዘጋጁ።
- ወላሂ አላችኋለሁ... ሳይኖረኝም ሳይኖርብኝም በመጣሁበት ሁኔታ ዱንያን በለቀቅኩ ብዬ ተመኘሁ።

ዱዓ ያስፈልገዋል ...

“እስቲ ዱዓ አድርጉ” ትል ነበር አታለም አላህ ይዘንላትና። ውድ እናት ነበረች። ምን ያረጋል አሷም ሞተች። ሌሎች ሰዎች እንደሞቱት ሁሉ ሞተች። ከሰው በልጦ ከሰው አኩል መሞት ያሳዝናል። ሌሎች በተቀበሩበት አፈርም ተቀበረች። ከሰው ልዩ ተሁኖ በሰው አቀባበር መቀበር ቅር ይላል። አላህ መታብሯን ብርሃን፤ መቀመጫዋን ጀነት ያድርገው። ታለም አፈን ከፍቼ የማዳምጣት አስታዋሼ ነበረች። ወንድ ይሁን ሴት ትልቅ ሰው አጠገብ መቀመጥ ትርፉ ብዙ ነው። በተለይ የአላህ ሰው ሲሆን። ትልቅ ሰው ትልቅ የሕይወት ካዝና ነው። ምድር ላይ ካሳለፈው ረጅም ሕይወቱ ዱንያን ለመጋፈጥ ስንቅና ትጥቅ የሚሆንህን ብዙ ነገር ያካፍልሃል።

ሞት ለሁሉ አኩል የሆነ ከስተት ነው። ጥሩ ነው ብሎ ዱንያ ላይ የተወው አንድም ሰው የለም። ሞት ምርጦች የተባሉትን ሁሉ ጨከኖ ወስዷል። ምርጡን መርጦ የሚተው ቢሆን ኖሮ ተወዳጃችን የአላህ መልዕከተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በቀሩልን ነበር። ምድር ላይ የደረሱብን መከራዎች ሁሉ ከርሳቸው ሞት አንፃር ምንም ናቸው። በርሳቸው ሞት በርግጥም ብዙ ተጎድተናል።

አላህን የማያወሳ፤ ነገሮችን የማያስተነትን፤ ዝምብሎ የሚኖር ፈዛዛ ሰው አትወድም ታለም። “ኤዲያ የማይረባ!” ትለዋለች።

“የዱዓ ሰው ናት” ይላታል የሰፈሩ ሰው ሁላ። መጥፎ ሰው ስታይ፤ መጥፎ ነገር ስታይ፤ መጥፎ አስተሳሰብ ስታይ፤ መጥፎ መሪ ስታይ፤ መጥፎ ባለሥልጣን ስታይ፤ መጥፎ ትውልድ ስታይ፤ መጥፎ ህልም ስታይ፤ መጥፎ ሁኔታ ስታይ... ሌላ ምንም ነገር አትናገርም። “እስቲ ዱዓ አድርጉ” ትላለች ተጨንቃ፤ ይኸው ብቻ ነው ጥያቄዋ።

እርጥብ ናት። ቀልቧ እርጥብ ነው። እጇ እርጥብ ነው። መከራ ወረደ፤ አሊያም ሊወርድ ነው በተባለ ጊዜ ሁሉ ጊዜ ሳትወስድ ፈጠን ብላ ዱዓ ታደርጋለች፤ ዱዓ ታስደርጋለች። ለዱዓ የምትሰስተው ነገር የለም። ለዱዓ ብላ ታርዳለች፤ ለዱዓ ብላ ሶደቃ ታደርጋለች።

እንደዛሬው ሰው ደረቅ አይደለችም ታለምዬ። ያለ ትርጉም የምትኖር አይደለችም። ሁሉን ነገር ታስተውላለች፤ በጥልቀት አርቃ ታያለች፤ ሁሉን ሚስጥር ለማንበብና ለመፍታት ትጥራለች፤ ለመተንተን ትታገላለች። ነገሮችን አናንቃ የተለየ ትርጉም ሳትሠጠው የምታልፍ አይደለችም። በሀሳብም በተግባርም ሁሌም ከአላህ ጋር ናት።

ለአላህ አብዝታ ያደረች ናት። ሁለመናዋ ከፈጣሪዋ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ በሁሉ ነገር ውስጥ የአላህን ሥራ በጥልቀት ታያለች። በውስጠ ልቦናዋ ትመለከታለች።

ጥሩ ነገሮች የተለወጡ እንደሆነ፣ ንፁህ የነበረው አየር ከደፈረሰ፣ ኑሮ ከተወደደ፣ ዝምድና ከተቆረጠ፣ መልካም ሁኔታዎች የተቀያየሩ ጊዜ፣ ከረምቱ ሲደርቅ፣ በጋው ሲዘንብ፣ ብርዱ ሲከፋ፣ ሐሩሩ ሲከብድ፣ ሰላሙ ሲጠፋ፣ ጥላቻው ሲንሠራፋ... የሆነ ነገር እንዳለ ትጠረጥራለች፤ በጉዳዩ ውስጥ የሰማዩ ባለቤት እጅ እንዳለበት ታስባለች። "ኧረ ዱዓ አድርጉ!" ብላ ታሳስባለች።

በሰው ልጅ ላይ የሚዘንቡ የምድር ላይ መከራዎች ሁሉ የሰው ልጅ የከፋት ውጤቶች እንደሆኑ ታምናለች። "እንደው ምን ታረገን ይሆን ጌትዬዋ!" ትላለች። ብቻዋን ታወራለች፣ ብቻዋን ትማፀናለች። "ኧረ እናንተ ሰዎች ይሄ ነገር ዱዓ ያስፈልገዋል!" ትላለች። "ዱዓ እናድርግ" ብላ ታስታውሳለች። ድንገት ብድግ ትላለች፤ ፈጠን ብላ ሽይኾችን አስጠርታ ዱዓ ታደርጋለች፤ አላህን ይፈራሉ ብላ ለምታስባቸው ደጋጎች ሁሉ ስለ ጉዳዩ ታሳስባለች። ዱዓ፣ ዱዓ፣ ዱዓ... ነው የሌት ተቀን ውትወታዋ። ያለ ዱዓ መኖር፣ ያለ ዱዓ መቆም፣ ያለ ዱዓ መውጣት፣ ያለ ዱዓ መግባት ይከብዳታል ለሷ ...

ዱዓ ምርኩዟ ነው፣ ዱዓ መደገፊያዋ ነው፣ ዱዓ ወንጭፏ ነው፣ ዱዓ ሰይፏ ነው፣ ዱዓ ጦሯ ነው፣ ዱዓ ጋሻዋ ነው።

እታለም የአምላኳ ጥገኛ ናት። ያለሱ መጠጊያ ምሽግም የላት። የሁልጊዜዋ ወሬዋ ከሱ ጋር ነው። ሹከሹከታዋ ወደሱ ነው። ምላሷ ከዚክር አያርፍም፤ ጣቶቿ ከሙሰቢሐ አይለዩም። ዕድሜዋ ቢገፋም ሰኞና ሐሙስ ትፆማለች፣ ዱሓ ትሰግዳች፣ የሆነ ልዩ ቀን፣ ልዩ ፆም ካለ አስታውሱኝ ትላለች።

እንዲሁ ዝምብላ ነገሮችን ችላ የምትልና የምትዳፈር አይደለችም ታለም፤ ትፈራለች። አላህን ትፈራለች። ድንገት ሁኔታዎች ልውጥውጥ ሲሉ ትደነግጣለች። ከሁሉም ቀድማ ፊቷን ወደ አላህ ታዞራለች። ዚክር ታበዛለች። ትመፀውታለች። ኢስቲግፋር ታዘወትራለች። ከዱዓ በላይ ምን አለ! ብላ ትጠይቃለች።

በርግጥም ከዱዓ በላይ ምን አለ!!። የሰማይ ቤት ወሬ እያነፈነፈች የምትኖር ትመስላለች ታለም። የሆነ መጥፎ ነገር ሊከሠት እንደሆነ ከሰማች አሊያም ወሬ ያመጡላት እንደሆነ ያንን ከፉ ወሬ በዱዓ ልትቆጣጠረው ትፎክራለች፤ "ቆይ ለሱም ዱዓ አለለት!" ትላለች። በዱዓ ትተማመናለች። በዱዓ ትዝታለች።

እጅግ በዱዓ አድራጊነታቸው ከምገረምባቸው ከተሞች መካከል አንዷ ጎንደር ናት። ብዙዎች የክርስቲያን አገር እንደሆነች ያስቧታል። ግና በርካታ ሙስሊሞች ይኖሩባታል። ትላልቅ ዑለሞች ይገኙባታል። ጎንደር የበረካ አገር ነው። የበረከቱ ሚስጥር ዱዓ ይመስለኛል። ሙስሊሞቿ በደግነታቸው አይታሙም። በየምክንያቱ ሶደቃ ያበዛሉ። ብሉልን ጠጡልን ይላሉ። ገርነት፣ መውደድ የሕዝቡ ባህሪ ነው። ከዚህም ባለፈ በዱዓቸው ይታወቃሉ። በዱዓቸው ይተማመናሉ። የሆነ ነገር መከሠቱን ከሰሙ፣ አሊያም ሊከሠት እንደሆነ መረጃው ከደረሳቸው፣ በየመስጊዱ ይጣራሉ፣ ይነግራሉ፣ ያስነግራሉ። ዱዓ እንዲያደርጉ ያሳውቃሉ። በየአካባቢው ዱዓ እንዲረግ ያሳስባሉ። ስለ ዱዓ አስፈላጊነት ይመክራሉ።

ጠላት እያሴረባቸው መሆኑን ካወቁ፣ አገር በበላእ ሊታመስ እንደሆነ ምልክቱ ከመጣላቸው፣ መረጃውም ከደረሳቸው፣ ዝም ብለው እጃቸውን አጣጥፈው አይቀመጡም፤ ተመቻችተው ጥልቅ እንቅልፍ አይተኙም። ሁሉን መጥፎ ነገር ማስቆምና መመለስ ወደሚችለው ወደ አምላካቸው አቤት ይላሉ። ሌቱን በዱዓ ያነጋሉ፤ ቀኑን በፆም ያሳልፋሉ፣ ወደ አላህ (ሱ.ወ.) ይዋደቃሉ፤ ወደ ፈጣሪያቸው ይማፀናሉ።

በበላእ ሰሞንም ሆነ አንዳች አሳሳቢ ነገር ሲያጋጥም እንደየበላው ሁኔታና ደረጃ ቀናትና ወራት ድረስ ሊዘልቅ የሚችል የዱዓ አዋጅ ይታወጃል። መሣሪያቸውን ያወጣሉ፣ መከላከያቸውን ይወጥራሉ። የዱዓ ሳምንትና የዱዓ ወር ይፀድቃል። ከዚያም ዱዓው በጥብቅ እና ከልብ ይደረጋል። የሚገርመው ምላሹም አይዘገይም። ዱዓው እየተደረገ ሳለ፣ የተመደቡለት ቀናት ሳይጠናቀቁ፣ ብዙም ሳይቆይ የድል ብሥራት ይመጣል። ሊቀሰቀስ የነበረው በላእ ይከሽፋል፤ የተነሳው በላእ መንገድ ላይ ይቀራል። የታሰበ የጥፋት ድግስ ይከሰማል። ጠላት መንገድ ላይ "እርሱ በርሱ" ተባላ የሚል ወሬ ይሰማል። እንዲህም ሆኖ በላው ተመለሰ ብለው ዱዓቸውን አያቆሙም፤ እጃቸውን አያወርዱም። እስከመጨረሻው በዱዓ ይፋለሙታል። በዚህ መልኩ ስጋት ይወገዳል። ፍርሃት ይነሳል። ሽብር ይገፈፋል። ውጤት ካገኙበት በኋላም ይደሠታሉ፤ አምላካቸውን አብዝተው ያመሰግናሉ።

"ጎንደር በዱዓ ነው" የሚል መፈክር ሁሌ እሰማለሁ። አዎ ጎንደር በዱዓ ነው። በሚደረጉ ተደጋጋሚ ዱዓዎች ብዙ ዙር በላዎች በዱዓ ሲከሽፉ አይቻለሁ። ያዝልን ሲሉ ይይዝላቸዋል፣ አንሳልን ሲሉ ያነሳላቸዋል፣ እንዳያየን እንዳይሰማን አድርገው ሲሉም ያደርግላቸዋል። በርግጥም የጎንደር ሙስሊም በዱዓ ነው። የአገሬው ሰው ሰው

ሊይነካም። የነኩትንም በዱዓው ብቻ ነው ልከ የሚያስገባው። እንከትከቱን የሚያወጣው። የአገፌው አማኝ ከአላህ ጋር ነው። አላህም ከነርሱ ጋር ነው።

ዱዓ ከመሣርያዎች ሁሉ የሚበልጥ ትልቅ መሣርያ እንደሆነ አምናለሁ። አላህ ከሠጠን ፀጋዎች ሁሉ ዱዓ ትልቁ ፀጋ ነው ብዬ አስባለሁ። ግና ይህንን መሣርያ አባከነነዋል። በአግባቡ አልተጠቀምንበትም። በትከከልም ሥራ ላይ አላዋልነውም። አስቲ ምን ያህሎቻችን ነን ቢያንስ ከሶላት በኋላ ትዕግስት አድርገንና ጊዜ ወስደን ለአምስት ደቂቃ ያህል ዱዓ የምናደርግ? ለራሳችን ጥቅም መሰሰታችን ያሳዝናል።

የታሰረ ማለትስ እጁ ከዱዓ የታሠረ ነው። የተነፈገ ማለትስ ዱዓ ከማድረግ የተነፈገ ነው። በርግጥ አላህ በልብ ያሰቡትንም ይሠጣል። ግና አላህ ባርያው እጁን አንስቶ ሲለምነው ይወዳል።

ዱዓ ምድር ከሰማይ የምትገናኝበት ገመድ ነው። ባሮች ከአምላካቸው ጋር የሚተሳሰሩበት ሠንሠለት ነው። እጃችንን ካላነሳን፣ በምላሳችን ካልተማፀንን ግንኙነቱ ይቋረጣል። ብዙ ነገር መተው እንችላለን። ዱዓ ግን ፈጽሞ አንተው። ከዱዓ አንዘናጋ። በዱዓ ሕያው እንሆናለን። በዱዓ የተመኘነውን እናገኛለን፤ ያለምነውን እናሳካለን፤ የጠፋብንን እናገኛለን፣ የጎደለብንን እንሞላለን።

ዱዓን ሲቸግረን ብቻ አይደለም ማድረግ ያለብን። ሲጨንቀን ብቻ አይደለም ወደ አላህ መሮጥ ያለብን። በዱዓ የሌለንን ብቻ ሳይሆን ያለንንም፣ ያልገባንን ብቻ ሳይሆንን የገባንን፣ የማንችለውን ብቻ ሳይሆን የምንችለውን ሁሉ ከአላህ እንጠይቃለን። ያለንን እንዲባርከልን፣ ያጣነውን እንዲለግሰን፣ ያለቀብንን እንዲተካልን እንማፀናለን። በዱዓ ስላለንበት ሁኔታ ሁሉ ለፈጣሪያችን እንገልፃለን። ከፍታና ዝቅታችንን፣ መውደቅ መነሳታችንን ሁሉ እናሳስብበታለን።

ዱዓ ለሰው ብቻ አይደለም ለሁሉም ነው። ለሰው ለእንሰሳም ነው። ለትዳርም ለብቸኝነትም ነው። ለአገርም ለዓለምም ነው።

ዱዓ ጥቅሙ ሰፊ ነው። ዱዓ የሚደረገውም ለራስ ነው። ሌሎች ስላላደረጉ ዱዓ አላደርግም አይባልም። ሌሎች ግድየለሽ ስለሆኑ ግድየለሽ መሆን አይገባም። ዓለም እንዲህ ችግሯ በዝቶ፣ ሁኔታዋ ከፍቶ፣ ሰላሟና ፍቅሯ ጠፍቶ... ባለበት ሁኔታ የኔ ዱዓ ምን ሊለውጥ ብሎ ማጣጣልም ሆነ ተስፋ መቁረጥ ልከ አይደለም፤ ተገቢም አይደለም። ችግሮች እንዲህ በገዘፈ መልኩ ሊከማቹ የቻሉት በኛው ጥፋትና

ቸልተኝነት ነው። እኔም፣ አንተም፣ አንቺም “ብቻዬን ጨኬ ምን ላመጣ!” ብለን እጃችንን አጣጥፈን በመቀመጣችን ነው። እኛ ካልጮኽን ሌላ የሚጮኽ ከየት ይምጣ ታዲያ?

ዱዓ ማድረግ ሁሌም ከአላህ ጋር የመሆን ምልክት ነው። ዱዓ እናድርግ -ከአላህ ጋር እንሁን፤ ወደ አላህ እንቅረብ።

ዱዓ፣ ያልቻልነውን ነገር ሁሉን ነገር ለሚችል ጌታ ማሳሰብ ነው። ማሰብም፣ ማሳሰብም ዱዓ ነው።

ዛሬ ላይ ዱዓ የማያስፈልገው ነገር ምን አለ ወዳጆቼ!!

አዎ ሁሉም ነገር ዱዓ ያስፈልገዋል።